# ኒዮሊበራሊዝም ለተፈጠረበት ኅብረተሰብም አልሆነ

የዓለም የኢኮኖሚ ቀውስ በተከሰተበት ወቅት መንስዔውን ለማወቅ በተደረገው ጥረት ብዙዎችን ያስማማው ጉዳይ የፋይናንስ ሥርአቱ ጫፍ በረገጠው የኒዮ ሊበራሊዝም አመለካከት የተነሳ የተፈጠረበት ችግር እንደሆነ ደርሰውበታል።

ኒዮሊበራሊዝም የፋይናንስ ሥርአቱ ላይ በቂና ትክክለኛ የመንግሥት ቁጥጥር እንዳይኖር የተከለው አመለካከት ለችግሩ መከሰት በመንስዔነት ይጠቀሳል። ይህ አመለካከት ባንኮች በአጭር ጊዜ ትርፍ ለማካበት የረጅም ጊዜ ውድቀት የሚጋብዝ ተግባር ውስጥ በሰፊው እንዲሠማሩም አድርጓል።

የበለፀጉት አገሮች ቀውሱ እንደተፈጠረ በተናጠልና በጋራ የተለያዩ ፈጣን እርምጃዎችን ወስደዋል። ባንኮች ከስረው እንዳይዘጉ መንግሥታትና ብሔራዊ ባንኮቻቸው በትሪሊዮን ዶላሮች የሚቆጠር ገንዘብ ለባንኮች መድበው እስካሁን እየተንገዳገዱ እንዲቆዩ አድርገዋቸዋል።

እርምጃው በተዘዋዋሪ መንገድ መንግሥታቱ የባንኮቹ ባለንብረት እንዲሆኑና የመውረስ (ናሽናላይዜሽን) ተግባር እንዲፈፀም አድርጓል። ይህ ብቻውን በቂ ሆኖ ስላልተገኘ መንግሥታቱ ባንኮቹን በጊዜያዊነት እንዲወርሱ፣ ባንኮቹ የሰጡትን ብድር ሰብስበው ወደ አንድ ባንክ እንዲያስገቡ፣ እነዚህ ባንኮች ቆሎ ብለው አገግመው በሂደት ወደ ግሉ ባለሃብት ተመልሰው እንዲሸጡ፣ መጥፎ ብድሮች የተከማቹበት ባንክ በተራዘመ ሂደት እየከሰመ እንዲሄድ የማድረግ አሠራር ነው። ሂደቱ ግን ትርፉ ለግል ኪሳራው ለጋራ የሆነ ነው።

ባንኮቹ አትራፊ በነበሩበት ወቅት በኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ መንግሥት ጣልቃ መግባት የለበትም ተብሎ ትርፉን የባንኮቹ ባለንብረቶች በገፍ ሲዝቁት ኖረዋል።

ባንኮቹ መክሰር ሲጀምሩ ግን ባንኮች ከተዘጉ ኢኮኖሚው ተንገራግጮ ስለሚቆም መንግሥት ወጪውን ሸፍኖ የከሰሩትን ባንኮች አድኖ አትራፊ መሆን ሲጀምሩ ለመሸጥ ነው የተንቀሳቀሱት። ኪሳራውን የሚሸከመው መንግሥት ማለትም ሁሉም ዜጎች ሲሆኑ ትርፉን የሚያገኙት ደግሞ ባለሃብቶች የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ጫፍ የረገጠው የኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ በፋይናንስ ሥርአት መስክ ውጤቱ ትርፉ ለግል፣ ኪሳራ ለጋራ ማድረግ ሆኗል።

በሁለተኛ ደረጃ ጫፍ የረገጠው የኒዮ ሊበራሊዝም አስተሳሰብ (ማርኬት ፈንዳሜንታሊዝም) መንግሥት የባንክ ባለቤት መሆን የለበትም ብለው መላው የዓለም መንግሥታት ባንኮቻቸውን ለግል ባለሃብቶች እንዲሸጡ ሲያስገድዱ ከርመው የቀበሩት ፈንጂ ሲፈነዳ ቀድመው ባንኮችን የሚወርሱት እነርሱው ሆነው ተገኝተዋል። መርሁ ዳገት መውጣት ሲያቅተው ሳያቅማሙ እዚያው አራግፈውት ዳገት መውጣቱን ቀጥለውበታል። ይላል ባንድ ወቅት አዲስ ራዕይ ላይ የወጣ ፅሑፍ።

ይህን ለማለት የተነሳነው ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በስፔን ማድሪድ ልማታዊ ፖለቲካ የአፍሪካን ዕድገት ቀጣይ ለማድረግ ባለው ሚና ላይ በተነጋገረው

ስብሰባ ላይ ያሰሙት ንግግር ነው። ኒዮ ሊበራሊዝም ሂዶ፣ ሂዶ ጫፍ ላይ ወጥቶ ሁሉም ነገር ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ ሆኖ በነፃ ገበያ ብቻ መመራት አለበት በሚለው አመለካከቱ የምዕራቡን ዓለም እንዴት እንዳናጋው ከላይ የተቀመጠው ፅሑፍ በሚገባ ያስረዳል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እንዳሉትም በእርግጥም የኒዮ ሊበራል አመለካከት ለራሱ ለተፈጠረበት ኅብረተሰብ ካመጣው ጣጣ ባሻገር ለአፍሪካም የፈየደው አንዳች ነገር የለም።

ስለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የኒዮ ሊበራል አመለካከት ከ30 ዓመታት በላይ አፍሪካን ቢመራም፤ በእስያ የታየውን ያህል ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ ሽግግር ሊያስመዘግብ አልቻለም ያሉት።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሰሞኑን በማድሪድ ከተማ የአፍሪካ ዕድገት ቀጣይ ለማድረግ ልማታዊ ፖለቲካ በሚኖረው ሚና ላይ ባተኮረውና 17 የአፍሪካና አውሮፓ አገሮች በተካፈሉበት መድረክ ላይ እንደተናገሩት የኒዮ ሊበራል አስተሳሰብ ለታዳጊ አገሮች በተለይም ለአፍሪካ የሚያስፈልጋትን ያህል ልማት ለማምጣት አልቻለም።

አመለካከቱ በአፍሪካ የሚያበቃበት ምክንያታዊ ጊዜ ላይ መድረሱንም ሳይጠቅሱ አላለፉም። የመርሁ ደጋፊዎች ሲሉ እንደቆዩትም ለአህጉሪቱ ሰላም፣ዴሞክራሲና ልማት ሊያመጣ እንዳልቻለ የስፔን ሶሻሊስት ፓርቲና አይዲያ የተባለው ተቋም ባዘጋጁት በዚሁ ስብሰባ ላይ አብራርተዋል።

"በመጀመሪያ መርሁ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን የሃሳቡ ጠንሳሽ በሆኑት ያደጉ አገሮችም ውድቀቱ እየተረጋገጠ በመሆኑ ነው። የተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ የኒዮ ሊበራሊዝም መርኅ ትክክለኛ አለመሆኑን በመላው ዓለም ፊት አጋልጦታል።ፈተናዎቹን ሊያቀልላት አለመቻሉን ያረጋገጠችውን አፍሪካን ጨምሮ። ከዚህም በተጨማሪ መርሁ እያከተመለት ያለው በአፍሪካ በአብዛኛው ተቆጣጥሮት የነበረውን ቦታ በማጣቱ ነው" ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ገልጸዋል።

በስብሰባው ላይ የተካፈሉት የታንዛኒያው ፕሬዚዳንት ጃካያ ኪክውቴ ልማታዊ መንግሥታት ለአፍሪካ ብቸኛ አማራጭ መሆናቸውን ማሳያዎችን ጠቅሰዋል።

"በአፍሪካ በአማካይ በየዓመቱ ከአምስት በመቶ በላይ ዕድገት እየተመዘገበ ነው። ለምሳሌ ታንዛኒያ ከስድስት በመቶ በላይ ዕድገት እያስመዘገበች ነው። ጎረቤታችንን ኢትዮጵያን ዕይዋት 10 በመቶ ዕድገት ማለት ክንፍ አውጥቶ እንደመብረር ያለ ነው" በማለት በበኩላቸው ተናግረዋል።

በአፍሪካ እየተመዘገበ ያለው ዕድገት ሁሉም የልማት አጀንዳዎች በአህጉሪቱ ፍላጎት ላይ እንዲመሰረቱ የግድ እያለ ነው ያሉት ደግሞ የስፔን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆሴ ሉዊስ ሮድሪጌዝ ዛፓቴሮ ናቸው።

"አፍሪካ አሁን ያለውን የኢኮኖሚ ቀውስ ከሌላው በተሻለ እየተቋቋመችው ነው። በዚህ አስቸጋሪ ሂደት ውስጥ እንኳን ያልተጠበቀ ዕድገት እያስመዘገበች ነው። ይህ ደግሞ የሆነ ለውጥ እንዳለ ያሳያል። በእርግጠኝነት ዓለም አፍሪካን ያማከለ የፋይናንስ መዋሪያ እንደሚያስፈልገው የሚያመላክት ነው" ብለዋል።

የስብሰባው ተሳታፊዎች የሰጡት አስተያየት በርካታዎቹ የእስያ አገሮች በየአሥር ዓመቱ ኢኮኖሚያቸውን በእጥፍ እያሳደጉ መሆኑን ነው የሚጠቁመው። አሜሪካና ብሪታንያ ግን አሁን ካሉበት ደረጃ ላይ እያሉ እስከ 60 ዓመታት እንደፈጀባቸው ተናግረዋል። የኢኮኖሚ ተንታኞች የልዩነቱ  ምንጭ ደግሞ የሚከተሉት የልማታዊና የኒዮ ሊበራል ፖለቲካና ኢኮኖሚ መርህ መሆኑን ይገልጻሉ።

በተለይም አሁን ልማታዊ ፖለቲካ ላለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት የድህነት መገለጫ በነበረችው አፍሪካም ታይቶ የማይታወቅ ዕድገት እያሳየ መምጣቱን ይጠቅሳሉ።

**ቀድሞ የማይታሰብ የነበረና ኒዮ ሊበራሊዝም አሮጌ አመለካከትና የቀውስ ምንጭ መሆኑ መገለፁ እንዲሁም ለአፍሪካ የዕድገት ጉዞ የማይጠቅም መሆኑ መመስከሩ በዓለም ዙሪያ በተጨባጭ ከታዩት ሁኔታዎች አንፃር የሚያንሰው እንጂ የሚበዛበት አይደለም።**